## ብርሃንና ጨለማ

አብርሃም በየነ

እንደ ቀን ብርሃን ጨለማ በውስጡ
ክስተቶች የሉትም ህሊና እሚሰርጡ
ቁልጭ ፍንትው ያለ የባዶነት ወማ
የሚታይ የሌለው ንፁህ ነው ጨለማ
ይህን ሀቅ ለማመን ህሊናው ያቅማማ
ዕውነቱን ለማግኘት ያለ አንዳች ተፅኖ
ወደ ውስጥ ይመልከት ዐይኖቹን ጨፍኖ።

## ወርቅና ጨርቅ

ዘርና ጥላቻ ሞት እየሰበቁ
አማራን በጅምላ ሲንቁ ሲንቁ
"ጨርቅ" ናችሁ ባሉት "አድጊ ወርንጭላ"
ክቡር አቶ መለስ የኋላ የኋላ
ከኛ አፈር አኖሩት የርስዎን "ወርቅ" ገላ።

## ፀሀይ

ጧት ጧት ስትወጣ የጎሕ ፈገግታዋ
ማታ ማታም ስትጠልቅ የወርቅ ግምጃዋ
በሰማይ ጠርዞች ላይ ተስሎ ውበቷ
ያድማስ ፈርጥ ይመስላል ፀሀይ ደም ግባቷ።

# ዋልድባ

ቅጥነቱ እንደ ጅማት ቅኝቱ እንደ ክራር

ስሩ እንደ ጠነነ እሾሁ እንደ ግራረ

የሚጨስ አንጀቱ ማዕጠኑ ከርቤ

አንድም ሌላ ካሳ አንድም ሌላ ውቤ

ዳግም ካልወለደ ደረስጌና ቋራ

ዋልድባም ይሆናል ዘግይቶ ሁመራ።

ጥቅምት 2005